# ከ3ኛ-12ኛ ክፍል ለሚገኙ ተማሪዎች የማህበራዊ እና ስሜታዊ ትምህርት (SEL) የዳሰሳ ጥናት ውጤቶች ላይ የወላጅ/አሳዳጊ አጠቃላይ ምልከታ፣

በ2022-23 የትምህርት ዘመን፣ የማህበራዊ እና ስሜታዊ ትምህርት (SEL) ጥናት ሁለት ጊዜ የተሰጠ ሲሆን፡-

- አንድ ጊዜ በበልግ (ከጥቅምት 24 - ህዳር 4/2022)
- አንድ ጊዜ በፀደይ (ከሚያዝያ 24-ሚያዝያ 28/2023)

የSEL ዳሰሳ ከ3-12ኛ ክፍል ላሉ ተማሪዎች የተሰጠ ሲሆን፣ በዳሰሳ ጥናቱ ላይ የተሳተፉ ተማሪዎች እና ቤተሰቦቻቸው ስለ ውጤታቸው የግል ሪፖርት ይደርሳቸዋል።

**SEL አስፈላጊ የሆነው ለምንድ ነው?** የማህበራዊና ስሜታዊ ትምህርት ተማሪዎች በትምህርት፣በስራ እና በግል ህይወታቸው ስኬታማ እንዲሆኑ የሚያግዙ አስተሳሰቦችን፣ ክህሎቶችን፣አመለካከቶችን እና ስሜቶችን ይገልፃል።

የዳሰሳ ጥናቱ የተማሪዎችን የSEL ችሎታዎች በአራት ክፍሎች መረጃ ለመሰብሰብ የሚጠቅም ሲሆን፣ የተገኙት ውጤቶች ወላጆች የልጆቻቸውን ወቅታዊ ጥንካሬዎች እና አስፈላጊ የሆኑ ክህሎቶችን የበለጠ ለማዳበር የሚረዱ ቦታዎች ምን እንደሆኑ የተማሪዎችን የተሟላ ምስል ለማሳየት የሚረዱ መሳሪያዎች ናቸው።

| የSEL የብቃት መስክ | መግለጫ |
|---|---|
| **የለውጥ አስተሳሰብ** | ተማሪዎች ለትምህርት ውጤታቸው ወሳኝ በሆኑት ጉዳዮች ላይ ለውጥ ለማምጣት አቅም ይኖራቸው እንደሆነ የሚያስችል ግንዛቤ ነው። |
| **ቁርጠኝነት** | ተማሪዎች የትምህርት ውጤቶችን በማሳካት ረገድ ምን ያህል እንደሚሳካላቸው ያምናሉ። |
| **እራስን ማስተዳደር** | ተማሪዎች ስሜታቸውን፣ ሀሳባቸውን እና ባህሪያቸውን በተለያዩ ሁኔታዎች እንዴት በጥሩ ሁኔታ እንደሚቆጣጠሩ። |
| **ማህበራዊ ግንዛቤ** | ተማሪዎች የሌሎችን አመለካከት ምን ያህል እንደሚገነዘቡ እና ትኩረት እንደሚሰጡ። |

## የተማሪዎን SEL የዳሰሳ ጥናት ውጤቶችን መረዳት፡-

እያንዳንዱ የዳሰሳ ጥናት ርዕስ በተማሪዎ ምላሾች ላይ ተመስርቶ ደረጃ ይሰጣል። የደረጃ አሰጣጥ ውጤቶቹ የተማሪዎን የጥንካሬ ደረጃ በእያንዳንዱ የርእሰ ጉዳይ ክፍል እንዲረዱ ያግዝዎታል። ሪፖርቱ ስለ ርዕሰ ጉዳዩ አጭር መግለጫ እና ክህሎትን ለመጨመር የሚወሰዱ እርምጃዎችን ያቀርባል።

| ደረጃ (1.0-5.0) | ምድብ |
|---|---|
| 4.3-5.0 | ከፍተኛ ጥንካሬ |
| 3.5-4.29 | ጥንካሬ |
| 2.0-3.49 | መካከለኛ ጥንካሬ |
| 2.0 በታች | ዝቅተኛ ጥንካሬ |
| "ደረጃ የለም" | ምንም ምላሾች አልተመዘገቡም። |

ስለ SEL የዳሰሳ ጥናት ውጤታቸው ከተማሪዎ ጋር ለመነጋገር አንዳንድ ጠቃሚ ምክሮች ከዚህ እንደሚከተለው ይቀርባሉ፡-

- በሁለቱም ጥንካሬዎች እና የእድገት ቦታዎች ላይ ማንፀባረቅ። ምክንያቱም እነዚህ እኩል አስፈላጊ በመሆናቸው።
- ሪፖርቱ "ውጤት" እንዳልሆነ ይልቁንም ልምዳቸውን ላይ እንዲያተኩሩ እድል የሚሰጥ መሆኑን አስገንዝቧቸው።
- የልጅዎን ሁኔታ ይከተሉ። አንዳንድ ተማሪዎች ስለ ስሜታቸው እና ልምዶቻቸው በግልጽ መናገር ይችሉ ይሆናል። ሌሎች ደግሞ አጠር ያሉ ውይይቶችን ማድረግ ወይም በምትወያዩበት ጊዜ ንቁ መሆን ያስፈልጋቸው ይሆናል። ውይይቱን አብረው በእግር ሲጓዙ ወይም በመኪና ውስጥ በሚያሽከረክሩበት ጊዜ ማድረግ ይችላሉ።
- በአዎንታዊ መልኩ ውይይቱን ይጨርሱ። "ተማሪዎቹ ስለራሳቸው ምን ተማሩ? ጥንካሬዎቻቸው ምንድን ናቸው? እርዳታ ከፈለጉ ማንን ሊጠይቁ ይችላሉ?" የሚሉ ጥያቄዎችን ጠይቁ።

ስለዚህ ሪፖርት ወይም የተማሪዎ ጥንካሬዎች እና ፍላጎቶች ላይ ጥያቄዎች ካለዎት፣ እባክዎን የትምህርት ቤቱን አማካሪ፣ የትምህርት ቤት የስነ-ልቦና ባለሞያ ወይም የትምህርት ቤት ማህበራዊ ሰራተኛን በማግኘት ጥያቄዎን ያቅርቡ።

እናመሰግናለን።
ታህሳስ 2022